# በአላህ ስም ለሚፈጸም ወንጀልና ጭፍጨፋ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ምን ይላሉ?

በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሰው ግፍና በደል መጠንና ድካ የለውም።ያለፉትን ስርዓቶች ትተን ለአለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ሥልጣኑን በጉልበት የያዘው ጎሰኛ ቡድን በሕዝቡ ላይ የፈጸመውና እየፈጸመው ያለው ግፍና በደል ሳያንሰው ፣ ወጣቱ ሰላም አገኘለሁ፣ኑሮየን አሻሽዬ ዘመዶቼን እረዳለሁ ብሎ ወደ ውጭ አገር ቢሰደድም ከመከራው አላመለጠም። በቆዳው ቀለምና በዜግነቱ በስደት አገር ከሚገጥመው መጠነ ሰፊ ችግር የበለጠ በእምነቱና በሃይማኖቱ ላይ የታወጀ ጦርነት ሰለባ ለመሆን በቅቷል።

አልካይዳና አይሲስ የተባሉት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች የሆኑት አክራሪና  አሸባሪ ቡድኖች ከመነሳታቸው በፊትም ሆነ በኋላ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ላይ የሚመዘዘው ሃይማኖትን የተላበሰ የጥፋት ሰይፍ እያደገ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም።

የአገሪቱን አንድነትና የሕዝቡን ሰላምና እድገት የማይወዱ የቅርብና የእሩቅ ጠላቶች በየሁኔታውና በየወቅቱ መልካቸውን እየቀያየሩ ሰርገው ለመግባትና ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ያልሞከሩበት ጊዜና መንገድ የለም።ያንን ሙከራቸውን ግን ኢትዮጵያዊው ሁሉ ሃይማኖትና ጎሳ፣ቋንቋና ክልል ሳያግደው ተባብሮ ለመመለስ ችሏል፣አገራችን እስከ አሁን ለመኖሯም ምክንያት የሆነው ይኸው የሕዝቡ አንድነት በመኖሩና  ሁሉም እስላሙም ሆነ ክርስቲያኑ ለሃገሩ ነጻነት በከፈለው መስዋእትነት ነው።

ከአሁንስ በኋላ ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን ነጻነትና አንድነት አስጠብቀው ለመኖር ይችሉ ይሆን?ይህንን ለመመለስ ያለንበትን ሁኔታ ማጤኑ ተገቢ ነው።ለአንድ አገር ዘላቂ ሰላምና ነጻነት ብሎም  አገራዊ አንድነት የሕዝቡ መተባበርና በአንድነት መቆም ወሳኝ ነው። በቋንቋ፣በክልል፣በጎሳ፣ በሃይማኖትና በፖለቲካ አስተሳሰብ ተለያይቶ እርስ በራሱ የሚናቆር ከሆነ አደጋ ለመመለስ ሳይሆን አደጋን ለመጋበዝ ምቹና ተባባሪ ይሆናል። ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባበታል እንዲሉ።

እርግጥ ነው የተለያየ የፖለቲካ አስተሳሰብና እምነት፣ባህልና ቋንቋ በአንድ አገር ውስጥ ለምን ይኖራል አይባልም። የሕዝቡን ሰላማዊ ኑሮ እስካላናጋ፣ተከባብሮና ለአገራዊ አንድነት አደጋ እስካልፈጠረ ድረስ እያንዳንዱ የሚፈቅደውንና የሚያምንበትን  የፖለቲካም ሆነ የሃይማኖት ተቋም መከተሉ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቱ  ነው።እስከ ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያዊ በእምነትና በባህሉ ብሎም በቋንቋው ሳይፈረጅ ለመኖር ችሏል።ያማ ባይሆን ኖሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚናገሩና የተለያዩ እምነቶች የሚከተሉ ዜጎች ባልኖሩ ነበር። እርግጥ ነው እድገታቸው እኩልና ተመጣጣን አልነበረም።ያ ደግሞ በሰፈኑት ስርዓቶች በተለይም በመሪዎቹ አመለካከትና ንቃት የተወሰነ እንጂ በተራው ሕዝብ ወይም ዜጋ ውሳኔ የተደነገገ አልነበረም፤ አሁንም አይደለም።ሕዝብ መርጦና ተቀብሎ ባላሰፈነው ስርዓትና መሪ በሚፈጸመው ስህተት ሊጠየቅ አይገባውም።

አገራችንንም ሆነ እኛን ኢትዮጵያውያንን ብዙ አደጋዎች ከፊታችን ተደቅነውብናል።ኢትዮጵያ አገራችን ከሌለች ኢትዮጵያውያንነታችን ያከስምና ነበር ወይም ነበሩ ሆነን የምንቀርበት የጥፋት አደጋው ብዙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በእምነታችን ዙሪያ የሚፈጸመው ወንጀልና ጭፍጨፋ አንዱ ነው።

ዓለምን በሽብር እየናጣት የሚገኘው በልዩ ልዩ ስም የሚንቀሳቀሰው አክራሪ የሙስሊም ቡድን የሚፈጽመው ወንጀልና ግድያ በአረብና በሙስሊም አገሮችና ሕዝቦች ላይ ብቻ ተወስኖ የቀረ

የሥልጣን ፉክክር የሚነዳው እና ዓለም አቀፋዊ ይዘት እንዳለው በሙስሊሞችና ሙስሊም ባልሆኑት ሕዝቦች ላይ ጭምር የሚፈጽመውን ግፍና ጭፍጨፋ የማያውቅ የዚች ምድር ነዋሪ የሆነ ሰው የለም።ጭፍጨፋው አገርና ዜጋ አይመርጥም። እነዚህ ስልጣንና ብር ያሳበዳቸው፣ በህይወታቸው ተስፋ የቆረጡ የተሰባሰቡበት ቡድን ሴት፣ ህጻን፣አሮጊት፣ሽማግሌ ወጣት ብለው አያዝኑም።እንኳንስ ለሌላው ቀርቶ ለቤተሰባቸው አይሳሱም።የነሱ ተከታይና አገልጋይ ያልሆነውን ሁሉ፣ አላህ አኩበር እያሉ አላህ አኩበር የሚለውንና የሚሰግደውን እስላሙንም ሳይቀር ያጭዱታል፣ በሚዘገንን መንገድ ይገሉታል፤እስላም ስለሆነ አይራሩለትም። ኢትዮጵያውያንም በተከታታይ የዚህ የግድያና ጭካኔ ሰለባ ሆነዋል።

የዛሬ ዓመት በሊቢያ ውስጥ ከሰላሳ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በክርስቲያንነታቸውና በኢትዮጵያዊነታቸው በኢሲስ ታርደው ደማቸው ከቀይ ባህር አሸዋ ላይ መፍሰሱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።አሁን ደግሞ በተመሳሳይ መንገድ በሊቢያ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ዳይስ ታክፊሪ የተባለው የኢስስ ክንፍ የሆነ አሸባሪ ቡድን ከአስራ ስድስት በላይ የሆኑትን ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በተመሳሳይ መንገድ በጥይትና በስለት አንገታቸውን በመቅላት ገሏቸዋል።

ሙሉ ታሪኩን በሚከተለው የድረገጽ መልእክት መረዳት ይቻላል።

http://www.zehabesha.com/daesh-executes-over-a-dozen-ethiopian-christians-in-libya/

ኢትዮጵያኑን ለዚህ አይነቱ አደጋ የዳረጋቸው በአገራቸው ላይ የሰፈነው ዘረኛ ስርዓትና ድህነት እንደሆነ ሁሉም ያውቀዋል። ጎሳ ተኮሩ መንግሥትና ችግሩ ቢወገድ፣ ሕዝቡ የእኔ ነው የሚለው መንግሥትና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ቢሰፍን ማንም አገሩን ጥሎ ለመውጣት አይገደድም ነበር።የስደት ሰለባ የሆኑት ኢትዮጵያውያን የአንድ ሃይማኖትና፣የአንድ ጎሳ አባሎች አይደሉም።በሳውዲ አረቢያና በሌሎቹ መካከለኛው ምስራቅ የአረብና ሙስሊም አገሮች ለአደጋ ከተጋለጡት ኢትዮጵያውያን መካከል አብዛኛዎቹ ከወሎ ክፍለ ሃገር የተሰደዱ ሙስሊም ህጻናት ልጃገረዶች ናቸው።ሙስሊም በመሆናቸው የአመጸኞች እጅ አልራራላቸውም።ኢስስም ሆነ ሌላው የሽብር ቡድን ከአመለካከቱ ውጭ የሆነውን ሙስሊም እንደማይምረው በተደጋጋሚ ታይቷል።ይህ የሽብር ሰንሰለት በአፍሪካ ውስጥ እየሰረገ በመግባት ተመሳሳይ ቀውስና ሽብር በመፍጠር ላይ ነው።ከሽብርተኞቹ ወጥመድ ውስጥ የሚገቡት አብዛኛዎቹ የግንዛቤ እጥረትና፣በኑሮ ተስፋ መቁረጥ ያደረባቸው ወጣቶች ናቸው።የዚህ አይነት ችግር ያለባቸው ኢትዮጵያንም ስለማይጠፉ በቅድሚያ አደገኛ መንገድ ውስጥ እንዳይገቡ መከላከል የሁሉም ድርሻ ነው።በተለይም ሙስሊም ወጣቶች በዚህ መርዘኛ እባብ ሊነደፉ የሚችሉበት መንገድ ሰፊ ስለሆነ ስለእስልምና እምነት ሃቀኛ ትምህርት የሚሰብኩ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን አደጋውን በግንባር ቀደምትነት ሊከላከሉት ይገባል፤ወጣቱ በዚህ በተሳሳተ የጥፋት ማእበል ውስጥ እንዳይገባ ሊመክሩትና ሊያድኑት ይገባል።

ኢትዮጵያዊ ሙስሊሞች በመብታቸው ዙሪያ ለሚፈጸመው በደል ድምጻቸውን ማሰማት ከጀመሩ ከአራት ዓመት በላይ ሆኗል፣መሪዎቻቸውም በእስር ቤት እየማቀቁ ነው።ይህን ግፍና በደል የሚፈጽመውን መንግሥት ሲታገሉ ክርስቲያኑና ሙስሊም ያልሆነው ወገናቸው ከጎናቸው ቆሟል፤ትግላቸውን ትግሉ አድርጎ ተሰልፏል፣በውጭ አገርም በየመድረኩ ድምጻቸውን አስተጋብቷል፤አሁንም እያስተጋባ ነው።የእኛ እንጂ የነሱ ብሎ ከዳር አልቆመም።

በክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመውና የሚፈጸመው ግፍ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ሊቆረቁራቸውና ሊሰማቸው ይገባል።በእምነታቸው ዙሪያ የሚደርስባቸውን የመንግሥት ተጽእኖ እንደሚያወግዙትና እንደሚታገሉት ሁሉ በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ላይ በአላህና በእምነታቸው ስም የሚፈጸመውን ግፍና ኢሰብአዊ ድርጊት ሊያወግዙትና

ከክርስቲያን ወገናቸው ጎን መሆናቸውን በይፋ ማሳየት ይገባቸዋል።በሌላው አገር የሚገኘው ሙስሊም "በእስልምና ስም እምነቴን አትጠቀሙበት"( Not In My Name) እንዳለው ሁሉ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችም "ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ወገኔን በሃይማኖቴ ስም አትጉዱት" ብለው ሊጮሁና አድራጎቱን ሊያወግዙ ይገባቸዋል። የነብዩ ሞሃመድን ትምህርትና ትእዛዝ በተግባር ሊተረጉሙት ይገባል።ለሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ ከክርስቲያኑ ኢትዮጵያዊ፣ለክርስቲያኑ ኢትዮጵያዊ ከሙስሊሙ ኢትዮጵያዊ የተሻለ አጋርና ወገን አይመጣለትም።የአንድ አገር ልጆች፣በአንድ አገር መሬት ተወልደው ያደጉ፣ሲሞቱም የአንድ አገር አፈር የሚለብሱ፣ የአንድ አገር ወንዝ ውሃ እየጠጡ ፣ተጋብተውና ተዋልደው የኖሩና የሚኖሩ፣ በአንድ አይነት ስርዓት እየተረገጡ ያደሩና የሚያድሩ ናቸው። አንዱ ከሌላው ተለይቶ የተጠቀመበት ስርዓት የለም።ክርስቲያን መሪዎች ለክርስቲያኑ ገበሬ አልራሩለትም።ፍዳውን ሲያሳዩት ኖረው አልፈዋል።አሁንም እያሳዩት ነው።ስልጣንና ጥቅም ሃይማኖትና ጎሳ አይለይም። ስልጣን ለመያዝ የሚሽቀዳደሙና የሚጥሩ ግን ሃይማኖትና ጎሳን እንደመሰላል ለጊዜው ሊጠቀሙበት ይችላሉ ።ያንንም በአገራችንና በሌሎች አገሮች እያየነው ነው።

የአንዱ ጉዳት ለሌላው ጉዳቱ ነው።ለጋራ ጥቅም በጋራ መቆምና መሰለፍ ይጠበቅባቸዋል።ለሁሉም አደጋ ያጋለጣቸውን ስርዓት ለመደምሰስና ሁሉም ተከባብሮ የሚኖርበትን ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመመስረት እጅ ለእጅ ተያይዘው ከመታገል የተሻለ ቁም ነገር የለም።

በዚህ አጋጣሚ በቅርቡ በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የራዲዮ ስርጭት የተላለፈውን ውይይት ለግንዛቤ አያይዤዋለሁና ጊዜ ወስዶ ማዳመጡ አይከፋም።ብዙ ትምህርት ይገኝበታል እላለሁ።ብሶታቸውን አዳምጦ ተገቢ መልስ መስጠት ከሁሉም ቀና አሳቢ ወገን ይጠበቃል። ስህተትም ከሆነ ማስተማርና ማረም ተገቢ ነው።አገራችን ላይ ከተደቀኑት ችግሮች አንዱና አሳሳቢው ስለሆነ ሊታሰብበት ይገባል።እነኢሲስም ሊገቡበት የሚችሉበት ቀዳዳ ሊሆን ስለሚችል ክፍተቱን መድፈንና በሩን መዝጋት ተገቢ ነው።መዘንጋት የሌለበት ግን በሰጥቶ መቀበል ጽንሰሃሳብ ማመን አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን ነው።መግባባትም የሚቻለው በዚሁ ጽንሰሃሳብ ከተመሩና ካመኑ ነው።

'Ethiopian Muslims Perspective, Ethiopia's Foreign Policy And The Myth Of Historical Enemies. (P 1)'

https://youtu.be/5f0u3Ub_vOw

ለስደትና ለአደጋ ሳንጋለጥ ተከብረንና ተከባብረን ለምንኖርበት አገርና ስርዓት በጋራ እንታገል!

ዘረኞችንና አክራሪዎችን በጋራ እንቋቋም!!

አገሬ አዲስ